# <u>*የቤተሰብ ህግ*</u>



የሰ/መ/ቁ. 21740

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አስረስ መስፍን ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በአማ/ብሔ/ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 04313 መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘታቸው ነው፡፡

የአሁን አመልካች ክርክሩ በተነሣበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ያቀረቡት አቤቱታም ባለቤቴ መ/አለቃ መኮንን ለማ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ስለሆነ ሚስትነቴ እና የልጆቼ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በዚሁ የወረዳ ፍ/ቤት በተቃዋሚነት ቀርባ ተከራክራለች፡፡ ያነሳችውም የመከራከሪያ ነጥብ አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን ሚስት አይደለችም፡፡ ሚስት እኔ ነኝ የሚለው ነው፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ካቀረበችው የሰው ማስረጃ፣ የፅድር ሰነድ እና የማኅበራዊ ፍ/ቤት ውሣኔ ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሚች ሚስት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የአሁን መልስ ሰጭ የሚች ሚስት መሆናቸውን በሥ/ፋ/መ/ቁ. 155/95 ያስወሰኑ ቢሆንም በፍ/መ/ቁ. 148/86 ባደረጉት ክርክር ጋብቻው የፈረስ መሆኑን ስለሚረጋገጥ የካቲት 01 ቀን 1993 ዓ.ም. ስለሚስትነት ማስረጃው

የሚገልፀው ውሣኔ በፍ/መ/ቁ 148/86 የካቲት 05 ቀን 1993 ዓ.ም. ጋብቻው ፈርሷል በሚል የተሰጠው ውሣኔ ይሽረዋል፡፡ ስለሆነም የአመልካችን ሚስትነት ተቀብዬ አጽድቂያለሁ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን መልስ ሰጭ የይግባኝ አቤቱታ ለከፍተኛው ፍ/ቤት በማቅረቧ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይግባኝ ባይ (የአሁን መልስ ሰጭ) የምትከራከረው የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን ሚስት አይደለችም በሚል በመሆኑና የእርሷንም ሚስትነት አስቀድማ ያረጋገጠች በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ ነጥብ ሆኖ መወሰድ ያለበት የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሚች ሚስት ናት ወይስ አይደለችም የሚለው ነው፡፡ ይህንንም በሚመለከት ሚስትነትን በሁኔታ ስለማረጋገጥ የሚደነግገው ሕግ በሚጠየቀው አኳኋን አላስረዳችም፡፡ ስለሆነም መልስ ሰጭ ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት አይደለችም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ግራ ቀኙ በክልል ጠ/ፍ/ቤት ተከራክረዋል፡፡ ይህ ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በተመሳሳይ መንገድ የይግባኝ ባይን (የአሁን አመልካችን) ሚስትነት ውድቅ ካደረገ በኋላ የወ/ሮ ውብነሽ ታከለን ሚስትነት ጉዳይ በሚመለከት ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ ከሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ጋር ባደረጉት ክርክር የጋብቻውን መፍረስ እና አለመፍረስ አስመልክቶ እንደገና በጉባኤ ታይቶ እንዲወሰን ተመርቶ እያለ በመካከል ሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ሚች በሞቱበት ጊዜ ወ/ሮ ውብነሽ ሚስት አልነበሩም ማለት አያስችልም፡፡ ስለሆነም የሚች ሚስት ናቸው የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር በይዘቱ



ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ ካደረጉት ክርክር የተለየ ባለመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን መልስ ሰጭ በተቃዋሚነት በጉዳዩ ቀርባ የተከራከረችው የአሁን አመልካች የሚች ሚስት አይደሉም የሚሉበትን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ መልስ ሰጭ ይህንኑ ክርክር ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የእራሳቸው የሚስትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ በግራ ቀኙ መካከል በተነሳው ክርክር ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነጥብ የአሁን አመልካች የሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ሊሆኑ የማይችሉበትን የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር በአሁን መልስ ሰጭ በኩል ቀርቧል ወይስ አልቀረበም? በተቃዋሚ በኩል ይህን መሰል ክርክር ካልቀረበስ የአሁን አመልካች የሚች ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበዋል ወይስ አላቀረቡም? የሚለው ነው፡፡ ከዚህ ነጥብ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከት መልስ ሰጭ ሚስት እኔ ነኝ በሚለው ላይ አትኩረው የተከራከሩ ከመሆኑ በቀር የአሁን አመልካች ሚስት ሊሆኑ ያልቻሉበትን ክርክርና ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ምንም እንኳ የእርሷ ሚስትነት ከክርክሩ አካሄድ አኳያ ጥያቄ ውስጥ የገባ ባይሆንም የአሁን አመልካች የሚች የመ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ የሚለውን አቤቱታ በዚያው ደረጃ ሊያቋርጥ የሚችል ክርክርና ማስረጃ ግን አላቀረበችም፡፡ ሰለሆነም የአሁን አመልካች የሚች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ለመሆኗ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርባለች? በሚለው ነጥብ ላይ ጉዳዩ የተወሰነ ነው፡፡ ይህንንም በሚመለከት በከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረቡት ምስክሮች ምንም እንኳ አመልካችና ሚች ባልና ሚስት ሆነው አብረው ሲኖሩ እናውቃለን በማለት ያረጋገጡ ቢሆንም ሲጋቡና የጋብቻው ሥርዓት ሲፈፀም ነበርን፤ እናውቃለን በማለት ያላስረዱ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ እንደሚደነግገው ሚስትነትን በጋብቻ ሁኔታ አስረድተዋል ማለት አይቻልም በማለት የሰጠው ድምዳሜ ይህንን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመተርጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 699/1/ የጋብቻ ጽሑፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ነው ሲል ከደነገገ በኋላ ሁለት ሰዎች የባልና ሚስትነት ሁኔታ አላቸው የሚባለው ባልና ሚስት ነን እየተባባሉ አብረው የሚኖሩ እንደሆነና ቤተዘመዶቻቸውና ሌሎችም ሰዎች በዚሁ ሁኔታ መኖራቸውን ሲያረጋግጡላቸው ነው በማለት ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በመሠረቱ ይኸው ድንጋጌ ግልጽ ነው፡፡ ሕግ ግልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ደግሞ የሕግ ትርጉም ሥራ እንደማያስፈልግ የሕግ አተረጓጎም ዘዴ ያስገነዝባል፡፡ በግልጽ በሕግ በተመለከተው አኳኋን አመልካች በማስረጃ ያረጋገጠች ለመሆኑ እራሱ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ትርጉም ሥራ እንዲገባ ምክንያት የሆነው በዚህ ድንጋጌ ቁጥር 699/2/ የተመለከተው በተለያዩ ሁኔታ ካልታየ በቀር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 708 ከተመለከተው ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት መኖር ከሚለው በምን ሊለይ ይችላል የሚለውን በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ አለ የተባለው ግንኙነት የሚመለከት ሁኔታ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 708 የተጠቀሰውን የሚመለከት ነው የሚባል ከሆነ ይህንን የማሳየት እና የመከላከል ተግባር የሚለየው በተከራካሪ ወገን ተግባርና ግዴታ ነው፡፡ ለዚህም ነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 700/2/ የባልና ሚስትነት ሁኔታ አለመኖሩንን ለመከራከር የሚቻለው የተከራካሪዎች ዘመዶች የሆኑ ወይም ያልሆኑ አራት የመከላከያ ምስክሮችን በማስመስከር ነው የሚለውን መደንገግ ያስፈለገው፡፡

ስለሆነም አመልካች /የአሁን/ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ ለሚደነግገው ሁኔታ የሟች የመ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ለመሆኗ በበቂ ሁኔታ ማረጋገጧ እየታወቀ ከላይ እንደተገለፀው አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በትክክል ካለመረዳት የተነሣ የሟች ሚስት መሆኗን አላረጋገጠችም በማለት ማስረጃው አግባብነት እንደሌለው ተደርጎ ሚስት አይደለችም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡



<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሟች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ናቸው፡፡ እንዲሁም ይኸው ፍርድ በውጤት ደረጃ መልስ ሰጭም የሟች ሚስት መሆናቸውን አረጋጋጭ ነው ብለናል፡፡
2. የአማ/ብ/ሕ/ክል መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 04313 በመስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት በቁጥር 01052 በሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፤ ይፃፍ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ